

Rev Yong Thang and wife
ሬቨረንድ ዮንግ ታንግና ባለቤታቸው

# የሬቨረንድ ዮንግ ታንግ ምስክርነት

## The Testimony of Rev Yong Thang

ሰው እየሞተ እያለ ምን እንደሚያጋጥመው ታውቃላችሁ?

ከሞተ በኋላ ወዲያው የሚያየው ምንድ ነው?

ከዚያ በኋላስ፥ ነፍሱ ወዴት ነው የምትሄደው?

እርሱ ሞትን አይቷል፥ሲያልም ገነትም ነበረ ከሞትም ተነሣ።

<u>መግቢያ</u>

ስሜ ዮንግ ታንግ ይባላል ከማያንማር (በርማ) (Myanmar (Burma))። የቺን ጎሳ አባል ነኝ። ይህ ጎሳ ከማያንማር ጎሳዎች አንዱ ነው። የመጣሁትም ከደሀ ባህላዊ ገበሬ ቤተሰብ ነው። በአፕሪል 3፣ 1958 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ተወለድሁ። በቺን ግዛት ውስጥ ትንሽዬ መንደር ውስጥ አደግሁ።

<u>ህይወትና የኋላ ታሪክ</u>

በቤተሰቤ ውስጥ ከነበረው የገንዘብ ችግር የተነሳ፥ 9ኛ ክፍል እያለሁ ትምህርቴን አቋረጥሁ። ከዚያም ከቤተሰቦቼ ጋር መሥራት ጀመርሁ። በዚያ ወቅት ቤተሰቦቼ የልማድ ክርስቲያኖች ብቻ ነበሩ። ከሞቱ በኋላ የት እንደሚሄዱ አያውቁም ነበር። ከጓደኞቼ አንዱ *"ዮንግ ታንግ፥ ከሞትህ በኋላ የት የምትሄድ ይመስልሀል?"* ብሎ ሲጠይቀኝ፥ ልመልስለት አልቻልሁም። ስሞት ነፍሴ ገነት ትሂድ ሲያል በራሴ እርግጠኛ አልነበርሁም።

ለእኔ ገነት ተረት ተረት (የማይመስል ታሪክ) ነበር የሚመስለኝ። ለመረዳት ከባድ ለመቀበልም አስቸጋሪ ነበር። **ኢየሱስ ክርስቶስን** እንደ **አዳኜ** መቀበል ምን ማለት እንደሆነ አልገባኝም ነበር።

በ1980፥ በፀደይ ወራት፥ በመንደራችን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊ ጉባኤ (ሴሚናር) ነበር። ጉባኤውን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻ ጀምሮ ታደምሁ። ከጉባኤውም በ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ስለመዳን አወቅሁ። በመንደሯ ሙሉ መነቃቃት (ሪቫይቫል) ነበረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ **ኢየሱስ ክርስቶስን** እንደ ግል **አዳኜ** በሙሉ ልቤ ተቀበልሁት።

በ1980 በጴንጤቆስጤ ቀን፥የመንደሩ ሰው ሁሉ ለሦስት ቀን ጾምና ጸሎት ወደ ተራራ ወጣ። በጾም ጸሎቱ የመጨሻ ቀን፥ የ**መንፈስ ቅዱስን** ኃይል ተለማመድሁ፥ ሰውነቴ ሁሉ "ሲሚሚቅ" ተሰማኝ። የማይነገር ሰላም ተሰማኝ፥ በልቤም እረፍትና ሀሴት። ከጥርጣሬም ጥላ ባሻገር አዲስ ፍጥረት እንደሆንሁና ዘላለማዊ ሕይወት እንደነበረኝ አወቅሁ። በጾምና በጸሎት፥ በ**ክርስቶስ** የመዳኔን ማረጋገጫ አገኘሁ። ስሞትም በገነት እንደምሆን ሙሉ መተማመን (ድፍረት) ነበረኝ።

<u>ከባድ ህመምና ሞት</u>

ትዳር ከያዝሁ ብዙም ሳይቆይ፥ እኔና ባለቤቴ ካላይ ውስጥ ወደሚገኝ ታያር ጎንግ መንደር ተዘዋወርን፥ በማያንማር ውስጥ የሳጋይ ግዛት አካል ሲሆን በዚያ በእርሻ ውስጥ እንሠራ ነበር። (Thayar Gong village in Kalay፣ Sagai province) ከጥቂት አመታት በኋላ አገስት 1984 መጀመሪያ አካባቢ፥ በጽኑ ታመምሁ። ለብዙ ቀናት የአልጋ ቁራኛ ሆንሁ ምግብም መብላት አልችልም ነበር። ባለቤቴ የተቻላትን ብትንከባከበኝም፥ ሁኔታዬ እየባሰ መጣ። ብዙም ልኖር እንደማልችል ስትረዳ፥ ለቤተሰብ አባላቶች፥ ዘመዶቼና ጓደኞቼ ሁሉ እንዲጎበኙኝና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያዩኝ በፍጥነት አሳወቀች። ስለሁኔታዬም በሰሙበት ፍጥነት ሁሉ መጥተው ጎበኙኝ። አገስት 13፥ከምሽቱ 1:00 (ሰዓት) አካባቢ፥የደም ዝውውሬ ትክክል እንዳልሆነ በሰውነቴ አወቅሁ። እሁድ ነበረና ሁሉም የቤተሰቤ አባላት፣ ዘመዶቼና ጓደኞቼ ከባለቤቴ በስተቀር ለምሽት የአምልኮ አገልግሎት ወደ ቤተክርስቲያን ሄደዋል። ባለቤቴም ደክሟት ስለነበር እንቅልፍ ወሰዳት።

ቀስ በቀስ በሰውነቴ ላይ አስገራሚ ለውጥ አጋጠመኝ። በጣም ተጨንቄ ነበርና "*ኦህ! ዛሬ የመጨረሻ ቀኔ ነው። በቅርቡ መሞቴ ነው።*" ብዬ አሰብሁ። የመሰናበቻ ቃል ልነግራት ባለቤቴን ለመቀስቀስ ፈለግሁ ነገር ግን ሀዘን እንዲሰማት ስላልፈለግሁ ሀሳቤን ቀየርሁ። የእግር ጣቶቼን ቅዝቃዜ ይሰማኝ ጀመር። ብዙም ሳይቆይ፥ እግሮቼ፥የእጄ ጣቶችና መላ ሰውነቴ መቀዝቀዝ ጀመረ።

ለመንቀሳቀስ ሞከርኩ ግን አልቻልሁም። በአዕምሮዬ ለራሴ እንዲህ አልኩ፡ "*ተመልከት! ሰውነቴ የማይንቀሳቀስ ሆኗል። ዓይኖቼን ማንቀሳቀስ አልችልም። አፌ ግጥም ብሎ ተዘግቷል። ሊከፈት አይችልም!*" ከዚያም ይህ የተለመደ ቅዝቃዜ እንዳልሆነ ተሰማኝ። እነዚህ የመሞት ምልክቶች ነበሩ። ሞትን ልቋቋመው (ልቃወመው) አልችልም።

ሆኖም ግን፥ የት ልሄድ እንደምችል አወቅሁ። በገነት ነው የምሆነው! ባለቤቴን እያየኋት፥ ቀሪውን ዘመኗን ብቻዋን በመሆኗ አሳዘነችኝ። ስለዚህ በህይወቷ ሙሉ እንዲንከባከባት (እንዲጠብቃት) ወደ **ያሑዋሕ** ጸለይሁ፡ ፡ ህይወቴንም በ**ኢየሱስ** ስም በ**ያሑዋሕ** እጅ አሳልፌ ሰጠሁ።

ትንሽ ቆይቶ፥ የተከማቸ ጥቁር ደመና ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። (ምንም እንኳን ከላዬ ጣሪያ ቢኖርም፥አልፎ ሰማይ በትክክል ይታየኝ ነበር።) ጥቋቁሮቹ ደመናዎች እየቀረቡኝ ነበር። ከአልጋዬ ሦስት ጫማ (90 ሴንቲሜትር አካባቢ) ያህል ርቀ ከአልጋዬ በላይ አረፈ። በዚያ ቅጽበት ነፍሴ ከሥጋዬ ተለየች።

<u>ወደ ገነትና ወደ ሲዖል መሄድ</u>

ወደታች ተመለከትሁና ሰውነቴ ከባለቤቴ አጠገብ ተኝቶ አየሁ። ሙሉ በሙሉ ህይወት አልባ ሬሳ ነበር! ሰውነቴ እንደሞተ በእርግጥ አውቄ ነበር። በድንገት፥ ረዣዥም አጋንንት ከየአቅጣጫው ሲመጡ አየሁ። በአልጋዬ ዙሪያ ተሰበሰቡና በሥጋዬ ላይ አፈጠጡ። ከዚያም ወደ ሰማይ ተመለከትሁና ጮኽኩ "*መላእክት! እባካችሁ በቶሎ ሰውነቴን ጠብቁት።*" **ያሑዋሕ** ይመስገንና ምንም እንኳን ምን ይመስሉ እንደነበር ባላውቅም፥ ስጮህ ተገለጡ። አምስት መላእክት ወዲያውኑ ሰውነቴን ለመጠበቅ ከገነት መጡ። በዚያው ጊዜ፥ በሰውነቴ ዙሪያ ተሰብስበው የነበሩት አጋንንት፥ በቅጽበት ተሰወሩ። በድንገት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ የነበረውን አስታወስሁ። '*ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?*' (ዕብራውያን 1:14)

ከዚያ በኋላ፥ ከፊቴ ምን እንዳለ ተመለከትሁ። በትላልቅ የእሳት ነበልባሎች የሚነድን ስፍራ አየሁ። አስፈሪ ነበር። ከእሳቱ፥ ሺሆች የጠፉ ነፍሳት ሲጮኹ አየሁ፥ "*እባካችሁ አድኑን! ይህ ቦታ ልንቋቋመው በጣም ከባድ ነው እናም በታላቅ ህመምና ስቃይ ውስጥ ነን።*" ሳያቸው፥ ልቤ በሀዘን ተወረረ። በድንገት፥ ከሰማይ እንዲህ የሚለኝ ድመጽ ሰማሁ። "***ይህ ሲዖል ነው!***" ስለሲዖል መኖር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንብቤአለሁ። አሁን 'ሲዖል' የተባለውን ቦታ በገዛ ዓይኔ አየሁት እናም የእውነት ነበር። እነዚህ ነፍሳት በእንደዚህ ዓይነት አስከፊ ስፍራ ለምን እንደሚሠቃዩ አሰብሁ። **ጌታም** ልቤን አወቀውና መለሰልኝ "***በዓለም በህይወት ሳሉ፥ እንደ ጌታቸው አልተቀበሉኝም። ከሞቱ በኋላ፥ ወዲያው ወደዚህ ስፍራ መጡ።***" ከዚያም ትልቅ ጥቁር ጉርጓድ አየሁ። በጣም ጥልቅና በኃያል ሊጠፉ በማይቻሉ እሳቶች ነበልባሎች የተሞላ ነበር። በጣም አስፈሪ ይመስላል። አንድ ድምጽ ተናገረኝ "***ይህ አንድ ቀን ሰይጣን የሚታሰርበት ገሀነመ እሳት ነው።***" ወደ ምድር ራቅ ካለ ከፍታ ላይ ስመለከት፥ ሰዎች ሲመላለሱ፥ ሲሠሩና ሲተኙ፥ ሲበሉና ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ አየሁ፥ በህይወታቸው መቼም የሚረኩ አልነበሩም። ይህም ወደ መረበሽ ይመራል ከዚያም በዝብርቅርቅታና መከራ ይፈጸማል። የእውነት ዓለም ለመኖር ጥሩ ቦታ አይደለም። በመከራ ውስጥ ስላለው ዓለም በልቤ ጥልቅ ሀዘን ተሰማኝ እናም የማይቆጣጠሩት እንባ በጉንጮቼ ይፈስ ነበር።

ከዚያም መላእክት ከሰማይ ወደ ምድር **ያሑዋሕን** እያወደሱ ሲመላለሱ አየሁ። ቀጥሎ፥ ጠንካራ የብርሃን ጨረር ከገነት ሲወርድ አየሁ። አንድ መልአክ ወደ ገነት ወሰደኝ። ወደ ገነት ስገባ፥ በሚገርም ሁኔታ ሺሆች ቅዱሳንን አየሁ። ነጫጭ ልብሶችን ለብሰውና እየዘመሩ ነበር "*ሃሌ ሉያ! አሜን! ያሑዋሕን አወድሱት!*" ወደ ገነት በመድረሴ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉልኝ። የእውነት ነክቶኛል። በምድር ሳለሁ፥ ማንም አላከበረኝም ትኩረትም አልሰጠኝም፥ምክንያቱም ተራ ገበሬ ነበርሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን መዝግቦታል "እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።" (ሉቃስ 15:10) በእርግጥም እውነት ነበር። በፍጹም ሀሴት ተሞልቼ ነበር።

በገነት ያሉት እያንዳንዳቸው በሀሴት የተሞሉ ነበሩ። ከዚያም ምንም ሀዘን፥ ህመም፥ ጭንቀት፥ ረሀብም ሆነ ድካም በገነት እንደሌለ ተረዳሁ። ገነት በ**ያሑዋሕ** ክብር የተሞላ ቦታ ነበረ።

አንድ ሰው በዚህ ምድር ላይ በአጠቃላይ ከ70 እስከ 80 ዓመት ሊኖር ይችላል። ማንም ምን ያህል ሊኖር እንደሚፈልግ መወሰን አይችልም። በ**ያሑዋሕ** እይታ በጣም አጭር ጊዜ ነው። ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊው ሊያውቀው የሚገባው ነገር ከሞተ በኋላ ወዴት እንደሚሄድ ማወቅ ነው። ሰዎች ለራስ ወዳድነት ጥቅም ለህይወታቸው ለፍተው ይሠራሉ ነገር ግን በኋላ ላይ ባዶ ሆኖ ያገኙታል። **ኢየሱስ ክርስቶስን** እንደ **አዳኝና ጌታቸው** አድርጎ የመቀበል አስፈላጊነት አያሳስባቸውም። በህይወታቸው ፍጻሜ፥ ነፍሳቸው ለዘላለም ያለ**ኢየሱስ** በሲዖል ትሰቃያለች።

ገነት ሀሴትና ሰላም የተሞላ በእርግጥም በውስጡ ለመኖር መልካም የሆነ ቦታ ነው። ምንም ቃል ገነት ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ ለመግለጽ አይችልም። በገነት ዙሪያውን ስመለከት፥ ምንም ፀሐይ፥ ጨረቃም ሆነ ኮከብ አልነበረም፥ ነገር ግን ሁሉም ስፍራ በ**ያሑዋሕ** ብርሃን ያበራ ነበር። ቦታው ሞቃት አልነበረም። ሰውነቴና መንፈሴ ሁለቱም በ**ያሑዋሕ** ብርሃን ሲበረቱ ተሰማኝ። ምንም እንኳ ቤተሰቦቼ፥ ባለቤቴና እህት ወንድሞቼ በምድር በህይወት ቢሆኑም፥ ወደ ዓለም ለመመለስ አልተመኘሁም ምክንያቱም ህመምና መከራ ከተሞላበት ዓለም ተለይቻለሁና ነው። ሰው በደስታ ዓለም ውስጥ ሆኖ ምን እንደሚሰማው በቃላት ለመግለጽ ለእኔ አስቸጋሪ ነበር።

**ጌታ ኢየሱስ** በድንገት መጣና የስጦታ ሳጥን ሰጠኝ። ለመቀበል ከጌታ ፊት አጎነበስሁ። ቀና ስል፥ ሄዶ ነበር። ከዚያም አንድ መልአክ የራሴን ነጸብራቅ ማየት ወደሚያስችል መንገድ ወሰደኝ።

መጽሐፍ ቅዱስ የገነት መንገዶች በወርቅ እንደተሠሩ ይጠቅሳል። እውነት እንደሆነ በገዛ ዓይኖቼ አየሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንኳ ከሺሆች ዓመታት በፊት ቢጻፍም አሁንም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ስለ ስነፍጥረት መዝግቦና ጽፎ ይዟል፤ ሲዖል፤ ሀላፊና መጪ ጊዜዎች ሁሉ። ለሰዎች መዳን በ**ኢየሱስ** እንደሚገኝ ይገልጻል። የማንም ታላቅ ሰው ወይም ፈላስፋ ሀሳብ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቃል እውነተኛ ነው። **ኢየሱስ** "***እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።***" ([ዮሐንስ 14፥6]) አለ።

ውድ ወዳጆች፥ **ያሑዋሕ** እኔን ከገነት ወደ ምድር የመለሰበት ምክንያት በገነትና በሲዖል ያየሁትን እንዳካፍላችሁ ነው። ገነትና ሲዖል የእውነት አሉ። በምንም መልኩ ከዋሸሁና ካታለልኳችሁ **ያሑዋሕ** ይፍረድብኝ!

መዳንን ያገኙ ዘንድ እያንዳንዱ በ**ኢየሱስ ክርስቶስ** እንዲያምኑ የ**ያሑዋሕ** መሻት ነው። **እርሱ** ማንም ለዘላለም በእሳት ባሕር እንዲያሳልፍ አይፈልግም። ስለዚህም፥ ይህንን ምስክርነት በጥንቃቄ እንድትመለከቱት አሳስባችኋለሁ።

በገነት በወርቁ መንገድ ላይ እየሄድሁ ሳለ፥ ባማሩ ጌጦች የተሠራ ደማቅ (የሚያበራ) ቤት አየሁ። በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ቤት ሊነጻጸረው አይችልም። ባየሁት ነገር ተወስጄ ነበር። ያኔ ነው፥ የ**ኢየሱስን** ድምጽ "***ይህ ቤት ለአንተ ነው፥ በዚህ ለዘላለም እንድትኖር እፈቅድልሀለሁ፣***" ሲለኝ የሰማሁት። ኦ፥ በጣም ነው የተደሰትሁት! የዘላለም ቤቴ ነው!

ከዚያም ወደ ቤቱ ሮጥሁና ወደ ውስጥ ለመግባት መግቢያ በር ፈለግሁ። ነገር ግን **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡ "***አይደለም፥ ዮንግ ታንግ። ገና ጊዜህ አይደለም። አሁንም እኔን ያልተቀበሉ ብዙ ሰዎች አሉ። ልትሄድና መጨረሻቸው በእሳት ባሕር እንዳይሆን ልታስጠነቅቃቸው ይገባል። እኔ ወደ ምድር የምመጣበት ጊዜ እየቀረበ ነው። (የእውነት) በጣም በቅርቡ እመጣለሁ። እስከዚያ ድረስ የብዙዎች ልብ በምስክርነትህ እንደሚለወጥና እንደሚቀበሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።***" ምንም እንኳን ወደ ምድር ለመምጣት ባልፈልግም፥ እንቢ ልለው (ላልታዘዘው) ግን አልፈለግሁም።

<u>ወደ ዓለም መመለስ</u>

በኋላ ላይ፥ አንድ መልአክ ከሚያምረው ቤቴ ወደ ዓለም መለሰኝ። ከዚያም ለሰዓታት ቀዝቅዞ ተኝቶ ወደነበረው በድን ተመልሼ ገባሁ። ወደ ሰውነቴ ከገባሁ በኋላ፥ መልአኩ እጇን ገፋ አድርጎ ባለቤቴን

ቀሰቀሳት። ነቃችና እኔን ለማየት ሻማውን ለኮሰች። ሰውነቴ እስካሁን ቀዝቃዛ ነበረ ምክንያቱም ለአስር ሰዓታት ያህል ሞቼ ነበር። የሞትሁ ስለመሰላት ጮክ ብላ ማልቀስ ጀመረች። በዚህም ምክንያት፥ በአቅራቢያው ያሉት (ጎረቤት) ሁሉ ተሰበሰቡና በዙሪያዬ ቆሙ። አንዳንዶች እያለቀሱ ነበር። ታላቅ ሀዘን ተሰማኝና ማልቀስ ጀመርሁኝ። ከዚያም ሰውነቴ ቀስ እያለ ሞቀ። እስካሁን እንዳልሞትሁኝ አወቁና ተጽናኑ። ባለቤቴ በደስታ ተሞልታ ወደ እኔ ለመቅረብ መጣች። ምግብና ውኃ አበላቺኝ። ከንጋቱ 11:00 ሰዓት ነበር ሰማዩም በርቶ ነበር። ከምሽቱ 1:00 ሰዓት እስከ የሚቀጥለው ቀን ከንጋቱ 11:00 ሰዓት ድረስ ሞቼ ነበር። ያየሁትን የሲዖልን አስፈሪነትና የገነትን ውበት ልረሳው አልችልም። ህልም ወይም ብዥታ አይደለም። ምንም እንኳን ያ ክስተት ከ20 ዓመታት በፊት የሆነ ቢሆንም፥ እስከአሁን ድረስ በአእምሮዬ ውስጥ ትላንት የተከሰተ ያህል በግልጽ ተቀምጧል።

ስለዚህም፥ ይህን ምስክርነት የጻፍሁት ሰዎች **ኢየሱስ ክርስቶስን** እንዲያውቁትና እንደ ግል **አዳኛቸውና ጌታቸው** እንዲቀበሉት ለዓለም ለማካፈል ነው።

ከዳንሁ በኋላ፥ እኔና ባለቤቴ ወንጌልን ለማካፈል ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ተጉዘናል። **የያሑዋሕንም ቃል** ለማወቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተን ተምረናል።

ማስታወሻ፡ መጋቢ (ፓስተር) ዮንግ ታንግ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተመርቀዋል እናም በአሁኑ ጊዜ በ**ያሑዋሕ መንግሥት** ውስጥ በመጋቢነት፥ በሰባኪነት፥ በአገልጋይነትና በወንጌላዊነት በማይንማር የሰሜን ሻን ግዛት ውስጥ እያገለገሉ ነው።

ውድ ወንድሞች፥ እህቶች፥ አገልጋዮች፥ ይህን ምስክርነት ካነበባችሁ በኋላ፥ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ቢኖራችሁ አልያም መጋቢ ዮንግ ታንግን በአካል ለመገናኘት ብትፈልጉ፥ ከተልዕኳችን ጋር ግንኙነት ተገናኙ። **የያሑዋሕን ቃል** ለማስፋፋት የምታደርጉትን አስተዋጽኦ ወይም ተሳትፎ እናደንቃለን።

ይህን ምስክርነት የሚያነብ ሁሉ **ኢየሱስ ክርስቶስን** እንደ ግል **አዳኙና ጌታው** አድርጎ እንዲቀበል እንጸልያለን።

ማያንማር የወንጌል ምስክርነት አገልግሎት
Myanmar Gospel Testimony Ministry
mgtm777@yahoo.com

ቀጣዩ ከዋናው ምስክርነት ውጪ የገባ ነው

ሕዝቅኤል 18:32፤ የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።

ዮሐንስ 3:16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

ሮሜ.10:9-11 ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። መጽሐፍ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና።

ሐዋርያት 2:38-39 ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።

**ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝና ጌታ ለመቀበል በዚህ ጸሎት ምሪት መሠረት መጸለይ ትችላላችሁ።**

*ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ስለኃጢአቴ ሁሉ እጸጸታለሁ፥ የምጸጸተውም አንተን ስለበደልሁህ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ ኃጢአቴን ይቅር እንድትለኝና ውድ በሆነው ደምህ እንድታነጻኝ፥ ስሜንም በሕይወት መጽሐፍ እንድትጽፍልኝ እጠይቅሀለው። አንተንም የግል አዳኜና ጌታዬ አደርጌ ወደ ህይወቴ እቀበልሀለሁ። በመንፈስ ቅዱስ አትመኝ። ወደ ህይወቴ ግባና ኑር እናም ከእርኩሰት ሁሉ ነጻ አውጣኝ። የሥጋዬን ምኞት ጥያለሁ፤ የቀደመውን ህይወቴን ትቻለሁ፥ እንዲሁም አንተን ደስ የማያሰኙህን ሁሉ፤ ዛሬ፥ ያሠሩኝ ሠንሰለቶች ሁሉ እንዲበጠሱ እናገራለሁ፥ ነጻ ነኝ፥ ምክንያቱም አንተ ነጻ አውጥተኸኛልና፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፥ አሜን።*

የያሑዋሕ ሰላም በልባችን ውስጥ ይሁን፥ እንዲሁም አስታውሱ፥ ስለኃጢአታችን የሚገስጸን መንፈስ ቅዱስ ነው፥ መንፈስ ቅዱስ ብቻ። ያሑዋሕ ይባርካችሁ። (አንጀሊካ ዛምብራኖ)

**ያሑዋሕ** יהוה () () : በዕብራይስጥ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የእሥራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ የኤልሻዳይ ስም ነው። ይህንም እጅግ እጅግ እጅግ የከበረ ፍጹም ቅዱስ ስም ጌታችንና አዳኛችን የያሑዋሕ ልጅና ቃል የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ መንፈሱ ለሚያፈቅሩት ልጆቹ አስታወቀው። יהוה

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com